

# ምርምርና ስርጸት

አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ለጥናትና ምርምር ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ከመንቀሳቀሱ ባሻገር እንደ አንድ ዋነኛ የእይታ አቅጣጫ ከያዛቸው ተግባራት አንዱ ነው፡፡ዩኒቨርሲቲው ጥናትና ምርምር በተቋማዊ ስርዓት እንዲመራ ማድረግና ዩኒቨርሲቲውን በተለይ ከውሃ እንዲሁም ሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር በተያየዙ ምርምሮች የብቃት ማዕከል የማድረግ ዓላማ አንግቦ እየሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ቅድሚያ ከሚሰጣቸው አራት የምርምር አቅጣጫዎች ማለትም፤

- ዓለም አቀፍ ደረጃ መጠበቅ፤
- ለማህበረሰብ ጠቀሜታ ያለው ማድረግ፤
- ለላቀ ምርምር ክፍት መሆን፤
- ለተመራማሪዎችና ለመምህራን የተመቻቸ የምርምር አካባቢዎችን መፍጠር፤ በሚያስችል መልኩ ትኩረቱን በማድረግ ይሰራል፡፡

በዩኒቨርሲቲው በመምህራን ከሚሰሩ የምርምርና ጥናት ሥራዎች በተጨማሪ በሰባት የምርምር ማዕከላት ስር በውሃ ሀብት፤ በብዝሃ ህይወትና ባህል፤ በደጋ አትክልትና ፍራፍሬ ፤ በማህበራዊና ሥነ ባህሪ እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች ጥናትና ምርምሮችን በቋሚ ተመራማሪዎች በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

ዩኒቨርሲቲው አገራዊና አለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው ጉዳዮችን ከግንዛቤ ያስገቡ የምርምር ዘርፎች በመለየት ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ብቻ ከ68 በላይ የጥናትና ምርምሮች በአካዳሚክ ዩኒት እና ማዕከል ደረጃ በተቋቋሙ ክፍሎች አማካኝነት ተሠርተው ለሚመለከተው አካል ቀርቧል፡፡ በ2005-6 ዓ/ም ከ28 በላይ የምርምር ውጤቶች በአገር አቀፍና አለም አቀፍ ጆርናሎች ላይ ታትመዋል፡፡

የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ተደራሽነት ማረጋገጥ ሌላው በዩኒቨርሲቲው ትኩረት የተሰጠው ተግባር ነው፡፡ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ከሚጠቀማቸው መንገዶች መካከል ወርክሾፖች፤ሲፖዚዬሞች፤ሴሚናርና የህትመት ውጤቶች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ለአብነትም በ2006 በጀት ዓመት ከ 6 በላይ ሀገር አቀፍ፤ክልላዊ እና በዩኒቨርሲቲው ደረጃ የተካሄዱ ሴሚናሮችን አዘጋጅቷል፡፡

በቀጣይም ዩኒቨርሲቲው በሚገኝበት አካባቢና በዞኑ በተለያዩ አካባቢዎች የምርምር ማዕከላትን በማቋቋም የጥናትና ምርምር አገልግሎቶችን መስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ላይ በስፋት በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በሁለንተናዊ መልኩ እየሰፋ ከመምጣቱ አንጻር በከተማው በተለያዩ አካባቢዎች በሚያካሂዳቸው ግንባታዎች የመሠረተ ልማት ሥራዎች የአርባ ምንጭ ከተማን የዩኒቨርሲቲ ከተማ እያደረገ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡ ይህን ሂደት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማምጣትም በአካባቢው በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚገኙ ውቴቶች የማላመድ፤በፈጠራ ፤በአስተሳሰብና የተለያዩ በጎ ተሞክሮዎችን በማስፋት በኩል የራሱን አሻራ በማስቀመጥ ላይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው በማህበረሰቡ ችግር ላይ ያተኮሩ ጥናትና ምርምሮችን በማከናወን ላይ ሲሆን ውጤቱን በመከተል በሚከናወኑ ተግባራትም ላይ ትኩረት በመስጠት ለሀገር ልማትና ዕድገት በሚውል መልኩ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡ ይህን ለማሳካትም የምርምር'መሠረተ-ልማትና የሰው ኃይል ማሟላት ላይም በስፋት መንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡



# አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ
# ባውሃ ሀብት ምህንድስናና አስተዳደር
# የልህቀት ማዕከል

ኮርፖሬት ኮምዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
ስቁ - 046 881 4986
ፋክስ ቁ. 046 881 49 64

email - amucorcom@amu.edu.et
IP phone 10306

## ዩኒቨርሲቲው ለአካባቢው ማህበረሰብ እያበረከታቸው ካሉ በርካታ አስተዋጽዖዎች መካከል በጥቂቱ፤

- የጎልማሶች ተግባር ተኮር ትምህርትና ሥልጠና አመቂ አፈጻጸም አስመዝግቧል፤
- በመረጃና ኮሚዩኒኬሽን ዳ/ጽ/ቤት በኩል በአካባቢው በሚገኙ የመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ባለሽቦና ሽቦ አልባ የኔትዎርክ ገመድ በመዘርጋት የኢንተረኔት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሙያዊ ድጋፍ አድርጓል፤
- በዞኑ ለሚገኙ ነዋሪዎች አገልግሎት የሚውል ነጻ የህግ አገልግሎት ማዕከል በመክፈት በፍርድ ቤት ችሎት የመከራከር አቅም ለሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ነጻ የህግ ድጋፍና የምክር አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፤

## ቅድመ ታሪክና .........

የዛሬው አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በ1979 ዓ/ም በውሃ ኢንስቲትዩትነት ሲቋቋም የአገሪቱን እምቅ የከርሰ ምድርና የገጸ ምድር ውሃን በአግባቡ መጠቀምን መሠረት በማድረግ ቢያኔው የውሃ ሃብት ኮሚሽን ሥር በመሆን ነበር የማስተማር ሥራውን አህዱ ብሎ የጀመረው፡፡

በወርሃ ግንቦት 1996 ዓ/ም/2004 እ.አ.አ መሠረተ ልማት በማስፋፋትና የአደረጃጀት ለውጥ በማድረግ ከኢንስቲትዩት ወደ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሊያድግ ችሏል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከምስረታው ማግስት ጀምሮ ሁለንተናዊ ለውጥ ከማስመዝገቡ ባሻገር በሁሉም የከተማዋ አካባቢዎች አዳዲስ ግቢዎችን በመገንባት ሰፊ የማስፋፊያ ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በተፈጥሮ ፀጋና በፍራፍሬ ሀብቷ በታደለችው አርባ ምንጭ ከተማ በአሁኑ ወቅት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ 5(አምስት) ግቢዎች አሉት፡፡

ዩኒቨርሲቲያችን በከተማችን ቀድሞ በተራራቁና ባለሙ ሰፊ ስፍራዎች በሚያደርገው መጠነ ሰፊ የማስፋፊያ ሥራ የተበታተኑትን መንደሮች አንድ በማድረግና በማቀራረብ የከተማውን ታላቅ የልማት ፍላጎትና የእድገት ጉዞ በማገዝና በማስዋብ ረገድ አይነተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡

- በደቡብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት አርባ ምንጭ ቅርንጫፍ ጣቢያ የራሱን የአየር ሰዓት በመከራየት ለማህበረሰቡ አስተማሪ የሆኑ ፕሮግራሞች በማስተላለፍ ላይ ሲሆን በተለይም በፕሮግራሙ ላይ «የህግ-መንገድ» በሚል ርዕስ ስለህግና ተያያዥ ጉዳዮች በስፋት ግንዛቤ እያሰጨበጠ መሆኑ፤
- በአርባ ምንጭና አካባቢው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ላሉ መምህራን ፤ የደቡብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት አርባ ምንጭ ቅርንጫፍ ጋዜጠኞች እና ሌሎች የህዝብ ግንኙነት ሙያተኞች የአቅም መገንቢያና ክህሎት ማሻሻያ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፤
- ከ “STEM Project” ጋር በመተባበር በውጤታቸው የተሻሉ በመለስተኛ እና በከፍተኛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተወጣጡ ተማሪዎች በክረምት ወራት በዩኒቨርሲቲው እንዲቆዩ በማድረግ የሂሳብ፣የሳይንስና የምህንድስና መሰረታዊ እውቀትን እንዲሁም ተግባራዊ ስልጠናዎችን ለተከታታይ ሁለት ዓመታት እንዲያገኙ ተደርጓል፤
- በዩኒቨርሲቲው የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በመሰልጠን ላይ በሚገኙ እጩ ሃኪሞች በአርባ ምንጭ ሆስፒታል በሚሰጡ የጤና አገልግሎት ላይ የራሳቸውን ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት ማህበረሰቡን በማገልገል ላይ ይገኛሉ፤
- በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የበጎ ፍቃድ የደም ልገሣ በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ፤መምህራንና ሠራተኞች መደረጉ

ዩኒቨርሲቲው በአርባ ምንጭ ከተማ በተለያዩ ውብ አካባቢዎች በመሰረታቸው አምስት ግቢዎች አገልግሎት እየሰጠ ሲሆን እነዚህ ግቢዎችም ስያሚያቸውን ያገኙት በአካባቢው ከሚገኙ የቱሪስት መስህቦች ነው፡፡ እንደ አቀማመጥ ቅደም ተከተላቸው ከዋናው ግቢ ጀምሮ ኩልፎ፤ ነጭ-ሣር ፤አባያ እንዲሁም ጫሞ በሚል ስያሜም ይታወቃሉ፡፡

በየጊዜው በሚያደርጋቸው ዘርፈ ብዙ የማስፋፊያ ስራዎች የተነሳ በሀገሪቱ ካሉ ግዙፍና አንጋፋ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል አንዱ መሆን የቻለው ዩኒቨርሲቲው በስድስት ኮሌጆች፤ በሁለት ትምህርት ቤቶች፤ በአንድ ኢንስቲትዩትና በአንድ አካዳሚ የተዋቀረ ነው፡፡

በእነዚህም አደረጃጀቶች ስር በ50 የቅድመ-ምረቃና በ40 የድህረ-ምረቃ እንዲሁም በአንድ የሦስተኛ ድግሪ (የዶክትሬት ዲግሪ) መርሃ ግብሮች የመማር ማስተማርና በሌሎች የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

- በአርብቶ አደር አካባቢ የሚገኙ ነዋሪዎችን ዘመናዊ የእርሻ አስተራረስ ዘዴ እንዲከተሉ በሚደረገው ጥረት ከክልሉ አርብቶ አደር ጉዳዮች ቢሮ ጋር በመተባበር በአነስተኛ መስኖ አስተዳደር የ 6 ወር ስልጠና በመስጠት ድጋፍ ማድረግ
- ዩኒቨርሲቲው ባስገነባቸው ደረጃቸውን በጠበቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች በአካዳሚው በኩል በአርባ ምንጭ ከተማ ለሚገኙ የስፖርት ክለቦች እንዲሁም ዞናዊና ክልላዊ የስፖርት ውድድሮች አገልግሎት በመስጠት ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረጉ፤
- ከነዚህም በተጨማሪ በዳይሬክቶሬቱ በኩል የአካባቢውን ስነ-ምህዳር ከመጠበቅ አንፃርም በምርምር የተደገፉ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ለአብነትም በአካባቢው በቅርበት ከሚገኙ ቀበሌያት በወዜና በሻራ ቀበሌያት የሚገኘውን የተራቆተ አካባቢና ለጎርፍ ተጋላጭ የነበረውን 1082 ሄክታር መሬት በአንድ አመት ውስጥ ወደ ቀድሞ ይዞታው በመመለስ አካባቢውን ወደ አረንጓዴ መቀየር ተችሏል፡፡

ይህን ህብረተሰብ ተኮር ተግባሩን ለወደፊቱም በተጠናከረ መንገድ ማስቀጠል የሚያስችሉ እቅዶችን ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡



## በውሃ ሀብት ምህንድስናና አስተዳደር የልህቀት ማዕከል

ዩኒቨርሲቲው አቅሙን ለማሳደግ እያካሄዳቸው ከሚገኙ በርካታ የማስፋፊያ ሥራዎች መካከል አንዱ አዳዲስ ካምፓሶች መክፈትን ያካተተ ነው፡፡ በዚህም ከአምስቱ ግቢዎች በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት በዞኑ ከሚገኙ ወረዳዎች አንዱ በሆነው የጎፋ ወረዳ አንድ ተጨማሪ ካምፓስ “ሳውላ ካምፓስ” በሚል ስያሜ ለመክፈት የመሠረት ድንጋይ ጥሏል፡፡

አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በአሁኑ ሰዓት 4600 የሚሆኑ ሠራተኞችን ያቀፈ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ከ1446 በላይ መምህራን ናቸው፡፡ ዩኒቨርሲቲው በመደበኛና ኢ-መደበኛ በሆኑ መርሃ ግብሮች በአጠቃላይ 21650 ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተናገድ ላይ ይገኛል፡